የትንሳኤ ቀን ከእሳት ነዋሪዎች እጅግ ዝቅተኛ ቅጣት ለሚቀጣው አላህ እንዲህ ይለዋል: "ምድር ውስጥ የሚገኙ ነገሮች ሁሉ ቢኖርህ ያንን ነገር ፍዳ ታደርገዋለህን?" እርሱም: "አዎን" ይላል።

ከአነስ ቢን ማሊክ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል፦ «የትንሳኤ ቀን ከእሳት ነዋሪዎች እጅግ ዝቅተኛ ቅጣት ለሚቀጣው አላህ እንዲህ ይለዋል: "ምድር ውስጥ የሚገኙ ነገሮች ሁሉ ቢኖርህ ያንን ነገር ፍዳ ታደርገዋለህን?" እርሱም: "አዎን" ይላል። አላህም "በአደም ጀርባ
እያለህ ካንተ ከዚህም ያነሰ ነገር ነበር የፈለግኩት: በኔ አንዳችንም አታጋራ ነበር ያልኩህ። አንተ ግን በኔ ማጋራትን እንጂ ሌላውን ነገር እምቢ አልክ።"»
[ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከእሳት ነዋሪዎች መካከል እሳት ከገባ በኋላ ዝቅተኛውን ቅጣት ለሚቀጣው አላህ እንዲህ እንደሚለው ተናገሩ: ላንተ ዱንያና በውስጧ ያሉ ነገሮች ሁሉ ቢኖሩህ ከዚህ ቅጣት ፋንታ እነርሱን ፍዳ አታደርጋቸውምን? እርሱም: አዎን ይላል። አላህም እንዲህ ይለዋል: በአደም ጀርባ ሳለህ እኔ ካንተ ጋር ቃልኪዳን ስወስድ የፈለግኩትና ያዘዝኩህ ከዚህም የቀለለውን ነገር ነበር። እርሱም በኔ አንዳችንም አታጋራ የሚል ነበር። አንተ ግን ወደ ዱንያ ያመጣሁህ ጊዜ ማጋራትን እንጂ እምቢ አልክ።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/8315